ኪንግደም ሳውድ ዐረቢያ
በእስልምና ጉዳዮች፣ ገንዘብ ስጦታ፣
ዳእዋና መምሪያ ሚንስቴር
የህትመትና ሳይንሳዊ ምርም
ድርጅት

# የሐጅ መርሖች

አዘጋጅ

ዶ. ሐቢብ ቢን መዐሳ አልሉወይሒቅ

آداب الحج باللغة الأمهرية

በአላህ ስም እጅግ በጣም አዛኝ በጣም ርህሩህ በሆነው፡፡

## ተቀባይነት የማግኘት ብስራት

አንተ የተባረክህ የሐጅ ተጓዥ ሆይ! ናፍቆቱ እያስገደደህ ወደሱ ለመሄድ በምትዘጋጅበትና የጉዞ ባልደረቦችህ የኸሊል«ነብዩ ኢብራሂም»ን ጥሪ አቤት በማለት ሽርጉድ በሚሉበት ጊዜ መመሪያህ ሊሆኑ የሚገቡ የሐጅ ጉዞ መርሖች እነዚህ ናቸው፡፡ እነሱም መመሪያ ደንብ ብቻ ሳይሆኑ ተቀባይነት የማግኘት ብስራትና የ«አላህ» ሥራን መውደድ ምልክቶችም ጭምር ናቸው፡፡ እነሆ ከዚህ ቀጥሎ እነዚህን መርሖችና ብስራቶች እናቀርባለን፡፡

---

## መርሕ አንድ

## ኢኽላስ«ሥራን ለአላህ ብቻ ማጥራት»

አዎ.. ኢኽላስ«ሥራን ለአላህ ብቻ ጥርት አድርጎ ማከናወን».. አንት የተባረክህ የሐጅ ተጓዥ ሆይ! አንተ «አሁን» ወደ አላህ ቤት እያመራህ ነውና የአላህን ወዴታ«ምንዳ» በአጽንኦት የምትፈለግ ሁን.. ከሱ ዘንድ ያለውን ሁሉ የምትፈልግ ሁን.. ለጥሪው አቤት ባይ ሁን..

ይህን ሁሉ መንገድ ቆርጠህና ይህን ሁሉ መከራ ተሸክመህ የዚህች ዓልም ክብር ወይም የገንዘብ ትርፍ እንዲሁም ከማነም ውዳሴ ወይም ምስጋና ፈላጊ እንዳትሆን ተጠንቀቅ። እንደዚህ ከሆንክ በነዚያ ተቀባይነት

ባገኙት እድለኞች ማህድር ውስጥ አትካተትምና..

ነገር ግን ይህን ታላቅ የአላህ ትእዛዝ በምንፈጽምበት ጊዜ እውነተኛ ኢኽላስ ለመጎናጸፍ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል??

እውነተኛ ኢኽላስን ይህን ታላቅ ሥራ ለመፈጸም ካሰብንበት ከመጀመሪያዋ ቅጽበት ጀምሮ «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» አላህን ከፊታችን በመደቀንና ልባችንን በሱ በመሙላት ልንጎናጸፈው እንችላለን።.. ለማንኛውም የዚህች ዓለም ኢላማ ፊትህን አታዙር።.. ይልቁንም ልብህን ሊሞላው የሚገባው «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» ለአላህ ጥሪ ሙሉ ታዛዥ መሆን ብቻ.. እንዲሁም

«ሙስሊም የተባሉት ሐዲስ ዘጋቢ ያሰፈሩት» “አንድ ኡምራ አስከዚያኛው ኡምራ ከመካከላቸው ያለውን ኃጢያት ያስተሰርያሉ ተቀባይነት ያገኘ ሐጅ ደግሞ ምንዳው ጀነት እንጂ ሌላ አይደልም” ከሚለውና «ቡኻሪና መስሊም» ካሰፈሩት “በዚህ ቤት ሴት ጋር ሳይገናኝና ሳያምጥ ሐጅ ያደረገ ሰው እናቱ በወለደቻው ቀን ወደነበረው ንጽህና ይመለሳል” ከሚለው ከነቢያችን ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም አባባል«ብስራት» እጣ ፋንታ እንዲኖረህ ተስፋ ማድረግ ነው።..

አዎ ይህ ዋና አላመህ ሊሆን ይገባል።.. ኢላምህ ሐጂ እገሌ አንዲትባል ወይም ሰው እንዲያሞግስህ መሆን

የለበትም፡፡..ይልቁንም ሙሉ ፍላጎትህ ተቀባይነት ማግኘትና የአላህ ውዴታ መሆን አለበት፡፡

## መርሕ ሁለት

## አገልጋይነትን በልብ ማስረጽ

መላው የሐጅ ሥራ ተጓዡ ከነየተበት«ካሰበበት» ጊዜ ጀምሮ ወደ ሀገሩ እስኪመለስ ደረስ ተውሂድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የሐጅ ሥራ ሀሉ.. እንቅስቃሴው ሁሉ.. ጸጥታው ሁሉ የአላህ ትእዛዝ ፍጸማ እንጂ ሌላ ነገር አይደለም፡፡.. አንተ የተከበርክ የሐጅ ተጓዥ ሆይ! ልብህን በነዚህ ነገሮች በምትሞላ ጊዜ.. ለታላቁ አላህ የመዋረድና የመገዛት ስሜት እንዲሁም ራስህን፣ አካላትህን፣ መላ ስሜትህንና ሕይወትህን «ልቅናና

ሞገስ ለሱ ይሁንና» ለአላህ አገልጋዮች የማድረግህ ስሜት በግልጽ ይሰመሃል፡፡ ያን ጊዜ የሐጅ ፍሬ በልብህ አብቦ ያፈራል፡፡ እናም ተቀባይነት ካገኙት ሰዎች መካከል አንዱ ትሆናለህ፡፡.. ከዚህ በፊት በፍርሃት ተሞልቶና የአላህን ትእዛዛት አክብሮ ለበይክ እያለ ወደ ሐጅ ሥራ የገባን የሐጅ ተጓዥ አይተሃል?? እሱና ለበይክ በማለት ብቻ ማንኛውንም የዚህች ዓለም ሥራ እንደሚሠራ ሁሉ ትእዛዛትን «በደመ ነፍስ»የሚፈጽም ሰው እኩል ሊሆኑ ይገባል? በፍጹም እኩል ሊሆኑ አይገባም፡፡.. አንተ የባርነትንና ለአላህ ትእዛዛት የመገዛት ጥልቅ ስሜት የሚሰማህ ከሆነ የመንገዱ ድካም፣ የመጨናነቁ ጣጣና የወጪ መከራ ምንም አይሰማህም፡፡

## ምርሕ ሦስት

### ወጭውን ከንጹህ ገንዘቡ ለይቶ መመደብ

አንተ የተከበርክ የሐጅ ተጓዥ ሆይ! ከኔ ጋር የሚከተለውን የነብያችንን ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ሐዲስ በጥሞና ተመራመር “አንድ የሐጅ ተጓዥ በጥሩ «ንጹህ» ገንዘቡ ወደ ሐጅ በወጣ ጊዜ ገና እግሩን ርካብ አስገብቶ ለበይክ አላሁመ ለበይክ በማለት ሲጣራ ከሰማይ በኩል የሚጣራው አንተ ሁልጊዜ ደስተኛ ትሆን ዘንድ ሐጅህ ተቀባይነት አግኚቷል.. ስንቅህ ከንጹህ ገንዘብ ነው.. መጓዣህም ከንጹህ ገንዘብ ነው.. ሐጅህ ንጹህ ከወንጀል የጠራ ነው፡፡ የሚል ጥሪ ያሰማል፡፡

እርኩስ በሆነ በእርም ሥራ በተካበተ ወጭ የወጣ «የሐጅ ተጓዥ» ደግሞ ገና እግሩን አርካብ አስገብቶ ለበይክ አላሁመ ለበይክ በማለት ሲጣራ ከሰማይ በኩል የሚጣራው ሐጅህ ተቀባይነት የለውም ደሰታም አታግኝ ስንቅህ በእርም ሥራ ከተካበተ ገንዘብ ነው:: መጓዣህም እንደዚሁ ሐጅህ በወንጀል የተሞላ ንጹህ ያልሆነ ነው የሚል ጥሪ ያሰማዋል" «ጦበራይ ዘግበውታል»

አዎ.. ለምን የፊተኛው የተቀባይነት ባለጣ ሆኖ፣ ሁለተኛው ሐጁ ፊቱ ላይ ተወረወረለት?? መልሱ: የፊተኛው እድሜ ልኩን በእርም ሥራ የተካበትን ገንዘብ አጥብቆ ይርቅ ስለነበር ነው:: በተለይም ደግሞ በሐጅ ወጪ:: ሁለተኛው

**ደግሞ በተከለከለው አራጣ፣ጉቦ፣ ዝርፊያና የእርም እቃ ዋጋ ገንዘብን አካብቶ ከሱም የሐጅ ወጭውን ያደረገ ስለሆነ ነው።.. የሐጅ ወጪ ምን ያህል አደገኛ መሆኑን ተገነዘብክ?? የዚያ የሀጅ ወጪ ምንጭ በእርም የተካበተ ገንዘብ ከተቀላቀለበት ሐጂው ተቀባይነት እንዲያጣና ወደ ባለቤቱ ፊት እንዲወረወር ያደርጋል። በመሆኑም አንተ የሀጅ ተጓዥ ሆይ የሐራም ገንዘብን አጥብቀህ እራቅ። የሐጅ ወጭህንም ከተባረከው ንጹህ ገንዘብህ መርጠህ አድርግ።**

## መርሕ አራት

## ተውባ«ጸጸት»

---

የተከበርከው የሐጅ ተጓዥ ወንዲሜ.. አንተ በሕይወትህ ትልቅ ለውጥ ወደሚያስከትል ተግባር እያመራህ መሆኑን እወቅ።.. በሱ ተቀባይነት ካገኘህ እናትህ እንደወለደችህ እለት ከወንጀል ንጹህ ሁነህ ወደምትመለሰበት የሐጅ ሥራ እያመራህ ነው።.. በሕይወትህ የሚከሰተውን ይህን ኃያል ለውጥ ከዚህ በፊት የተፈጸሙ ወንጀሎችን በሚያብስ ንጹህ በሆነ ጸጸት ብትቀበለው ምንኛ ጥሩ ነው።..ታለቁ አላህ እንዲህ ይላል “ምእምናን ሆይ! ትድኑ ዘንድ ሁላችሁም ወደ አላህ«በመመለስ» ተጸጸቱ” ማንኛውም ሙእሚን በማንኛውም ሁኔታ ወደ አላህ በመመለስ እንዲጸጸት«ተውበት እንዲያደርግ» ታዙዋል። እሱ

በተለይም በዚህ መሰሉ አቋም ተውበት እንዲያደርግ በጥብቅ ታዙዋል:: ጸጸትም«ተውበት» እውን ሊሆን የሚችለው ከማንኛውም ወንጀልና አመጥ በመውጣትና እርግፍ አድርጎ በመተው፣ ባለፉት ሁሉ ወንጀሎች በመጸጸት፣ ወደነሱም ላለመመለስ ቁርጠኛ በመሆን፣ በበደል የተወሰደን ገንዘብ በመመለስና ክብር ነክ በደሎችን ይቅርታ ጠይቆ ነጻ በመሆን ነው:: አንት የተከበርክ የሐጅ ተጓዥ ሆይ! ይህን ታላቅ ሥራ ለማከናወን ስትዘጋጅ ይህንን ካደረግህ«ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» በጌታህ ፈቃድ ተቀባይነትን ፈጽሞ አትነፈግም::

## መርሕ አምስት

## ደግ ጓድን መምረጥ

ተቀባይነት ወደ ማግኘት ብስራት ከሚያደርሱህ ነገሮች እጅግ ታላቁ ወደ ደግ ነገር የሚመረህንና ለደግ ሥራም የሚያግዙህን ደጋግ ጓዶች መምረጥ ነው፡፡ እነሱ በንጹህ ሐጅ ጉዞህ ከአጋዦችህ ሁሉ በላጮቹ ናቸው፡፡ ጓዶች..በመላው የሐጅ ሥራ ሁሉ በነብያችን ፈለግ መስመር እንዲትጓዝ ያደርጉሃል፡፡ እጆቻቸውም ወደ መልካም ነገር ሁሉ ይመራሉ፡፡.. እነዚያ ጓዶች ከፍተኛ ዋጋ ያለቸውን የሐጅ ጊዚያቶች በጨዋታ፣ በከንቱ ወሬና በተከለከሉ ነገሮች በመዘፈቅ የማያጠፉ ደጋግ ጓዶች ናቸው፡፡.. ጓዶች የሐጅ ሥራዎቻቸው ከመመሪያ ውጭ ከሆኑ ተግባራትና ከመስመር ከመውጣት ነጻ

መሆናቸውን በአጽንኦት የሚከታተሉ ናቸው።..ጓዶች የአላህን ትእዛዛት የሚያከብሩና ወሰኑን የማይተላለፉ ናቸው።.. ጓዶች የጌዞን ደንብና የታወቁ ዱኣዎችን «ጸሎቶች» ወሰን ያለመተላለፍ የሚጠብቁ ጥንቅቆች ናቸው። እንዲሁም የአላህ ልኡካንና እንግዶች መሆናቸውን በመገንዘብ ይህን እጅግ ታላቅ ክብር ያለውን ቦታ በጨዋታና በከንቱ ነገር እንዲሁም አድሚ በሆነ ግርግር የማያራክሱ ናቸው። ጓዶች ወደ አላህ ወዴታ የሚያደርሳቸውን ሐጅ የሚያደርጉ ናቸው። አዎ እነዚያ በኮሚቴም ሆነ ከዚያ ባነሰ ቡድን አብረዋቸው ሐጅ ሊያደርጉ የተገቡ ጓዶች ናቸው።

## መርሕ ስድስት

---

## የሐጅ ሥራን ህግጋት ማወቅ

አንተ የተባረክህ የሐጅ ተጓዥ ሆይ! ከወንጅል የጠራ«መብሩር» ሐጅ ለማግኘት ከሚያስፈልጉህ ነገሮች እጅግ ታላቁ የሐጅ ሥራን ህግጋት ማወቅ ነው:: ይህውም በሙሉ ግንዛቤና እውቀት አላህን መገዛት እንዲትችልና ሐጅህን ሊያበላሹ ከሚችሉ ስህተቶች ላይ እንዳትወድቅ ያግዝሃልና ነው::..ይህም እውን የሚሆነው የነብያችንን ፈለግ የሚከተሉ መሆናቸው የታወቀላቸው ታማኝ የሆኑ የእውቀት ባለቤቶችን «ኡለሞች» በመጠየቅ፣ እንዲሁም በሐጅ መስክ የነብያችንን ሰለላሁ አለይሂ ሰለም መምሪያዎች ያካተቱ፣ የሀጅን ማእዘናት፣ ግዴታዎችና ሱናዎች ሲያብራሩ

ማጣቀሻቸውን ቁርኣንና የነብያችን ሐዲስን ያደረጉ፣ ከህጉ ደንብ ውጭ የሆኑ የተጠሉ ተግባራትን የሚርቁና እነሱንም የሚከለከሉ የሐጅ ሥራ ህግጋት መጽሐፎችን በማንበብ ነው፡፡

## መርሕ ሰባት

## ትእግስት

ትእግስት.. ከምእምናን ባሕርያት እጅግ ታላቁ ነው፡፡ ለዚህም ነው ታላቁ አላህ እንደዚህ ያለው፡፡ “ታጋሾች ምንዳቸውን የሚሰጡት ያለግምት ነው” ትእግስት በመላ ሕይወቱ ከሙእሚን የማይለይ አብሮት ተጓዥ ቢሆንም በሐጅ ጊዜ እጅግ ታላቅ በሆነው ገጽታው ጎልቶ ይታያል፡፡ እውነተኛ ሙእሚን

የሆነው የሐጅ ተጓዥ ለጉዞ መከራና ጭንቅ ራሱን ያዘጋጃል፡፡ ያንም ሲያደርግ «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» ከአላህ ዘንድ ሚዛን ከሚያከብዱ መልካም ሥራዎቹ እንዲካተትለት ተስፋ ያደርጋል፡፡ በሙቀት ወይም በምግብ እጥረት እንዲሁም በመንገዱ እርዝመት አይነጫነጭም፡፡ ሥራውን በመመጣደቅ፣ በማስከፋት፣ በልብ ጥበት፣ በእጁና በምላሱ ሙስሊሞችን በመጋፋት አያበላሽም፡፡ ሰዎች በሚፈጥሩት መጨናነቅ፣ በሥራዎች መደራረብ፣ ሥራዎችን ሲፈጽም በሚደርስብት ስቃይ አይበሳጭም፡፡ ለሽርሽርና ለመዝናናት አንዳልሄደ፣ ይልቁንም የታላቁ አላህ ውዴታን በመፈለግ የሄደ መሆኑን ይገነዘባል፡፡

«ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» ለአላህ ትእዛዛት መፈጸም መታገስ ከትእግስት ዓይነቶች ሁሉ እጅግ ታላቁ መሆኑንም ያውቃል:: እንዲሁም የትእግስት ምንዳን ተስፋ የማድረግና «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» አላህ በመጨረሻው አገር የገባልን ቃል መረጋገጡን ከማየት ምልክቶች ታላቁ መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል:: ስለዚህም ይታገሳል ይታገሳል.. ምስጉንዋም ፍጻሜ ለጥንቅቆቹ ናት::

---

## መርሕ ስምንት

### የአላህን የሃይማኖት ምልክቶች«የአገልግሎት ገጽታዎች» ማክበር

ታላቁ አላህ እንደዚህ ይላል "«ነገሩ» ይህ ነው ያአላህንም የሃይማኖት ምልክቶች የሚያከብር ሰው እርሷ ከልቦች የሆነች ጥንቃቄ ናት" «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» የአላህን የአገልግሎት «ኢባዳ» ገጽታዎች ማክበር ከእውነተኛ ጥንቃቄ «ተቅዋ»ምልክቶች እጅግ ታላቁ ነው:: አንተ የተከበረክ የሐጅ ተጓዥ ሆይ! ወደ አላህ ቤት ልብህ ናፍቆትና አክብሮት ተሞልቶ ስትመጣ በነሱ

**የነብያችንን ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ፈለግ በመከተል የአላህን የኢባዳ ገጽታዎች ማክበር ይኖርብሃል፡፡ ግርማ ሞገሳቸውን በልብህ በማጉላት ልታከብራቸው ይገባል፡፡ የአላህን የኢባዳ ገጽታዎች «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» አላህ ከከለከለው ነገር ዐይንህን በማራቅ፣ እርም ያደረጋቸውን ነገሮች በመጠንቀቅና ሐጅህ በጀርባህ የመትሸከመው ታላቅ ኃጢያትና ወንጀል እንዳይሆንብህ ምላስህንና መላ አካልህን ከወንጀል በመጠበቅ ልታከብራቸው ይገባል፡፡ «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና« የአላህን የኢባዳ ገጽታዎች በመልካም ምግባር ለሙስሊሞች ወለታ በመዋል ልታከብራቸው ይገባል፡፡ «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» የአላህን የኢባዳ ገጽታዎች «ልቅናና ሞገስ ለሱ**

ይሁንና» የአላህን ባሮች ባለማስከፋት፣ ወደ አላህ በመጥራት፣ ሙስሊሞችን በመምከር፣ በተቻለህ መጠን እነሱን ስለሃይማኖታቸው፣ ስለመሰረተ እምነታቸው«ዓቂዳቸው»፣ ስለአገልግሎታቸውና ስለመዋዋያቸው በማስተማር ልታከብራቸው ይገባል።

## መርሕ ዘጠኝ

## መልካም ምግባር

የተከበርከው የሐጅ ተጓዥ ወንዲሜ.. «መልካም ምግባር» ከተባለው ታላቅ ባሕርይ ጋር ራስህን አለማመድ። እሱ «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» ለአላህ ውዴታና በዚህ በተባረከው ጉዞህ ካንተ ሐጅህ ተቀባይነት ለመጋኙቱ ምክኒያት ይሆናልና። መልካም

ምግባር «ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና» በአሳህ ቤት ሐጅ ለማድረግ በጉዞ ላይ ላሉ ወንድሞችህ ውለታ እንዲትውል ያነሳሳሃል፡፡ ከነሱ ደካማውን በመደገፍ፣ ገንዘብ ያጠ ረውን የገንዘብ እጥረቱን በመሸፈን፣ የሰው ያለህ ለሚል ተበዳይ በመድረስ፣ የጠፋን ሰው መንገድ በማሳየት፣ ለቁስለኛ የመጀመሪያ እርዳታ በማድረግ፣ እዝነትና ርህራሄ በማሳየት ውለታ ትውልላቸዋለህ፡፡.. እንዲሁም እነሱን ከማስከፋት በመቆጠብ፣ ከማጨናነቅ በመራቅ፣ ስህተታቸውን በትእግስት ተቀብለህ በማሳለፍ፣ አላዋቂዎች ቢያስከፉህ በመቻል ውለታ ትውልላቸዋለህ፡፡ አሁንም ለነሱ በፊትህ መልካም ፈገግታ በማሳየትና በርካታ በሚያበራ

ፊትህ ውለታ ትውልላቸዋለህ፡፡ መልካም መግባር የመልካም ሥራ ምእራፎችን በሙሉ ያካተተ ነው፡፡ በእውነት ምግባረ ስናይ እጅግ ጎልቶ የሚታየው ደግሞ «በዚህ ቦታ» ረጋ በማለት፣ ባለመቻኮል፣ ሰዎችን ከራስ በማስቀደምና ለሙስሊም ወንድምህ ለራስህ የምትወደውን ነገር በመውደድ ነው፡፡ የሚቻኮል፣ ሰዎችን የሚያጨናንቅ፣ ስርኣት የማይጠብቅ፣ ለደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች ርህራሄ የሌለውና በሐጅ ሥራው ሁሉ «ራሴ ራሴ» ማለትን መርህ ያደረገ የሐጅ ተጓዥ ከመልካም ምግባር «ፍሬ» ምንም ዓይነት እጣፋንታ የለውም፡፡ «ተቀባይነት ያለው» ንጹህ ሐጅ ደግሞ የመልካም ምግባር «ጣፋጭ» ፍሬ ነው፡፡

## መርሕ ዐሥር

## አዲስ ሕይወት የመጀመር ቁርጠኝነት

ከሐጅ ስርኣቶች መሳካትና ተቀባይነት ከማግኘቱ ብስራቶች እጅግ ታላቁ.. መጀመሪያ ሐጅን ካሰብክባት ጊዜ ጀምሮ ወደ ሀገርህ እስከምትመለስበት ጊዜ ድረስ ከሐጅ በኋላ አዲስ ሕይወት ለመጀመርና ከሐጅ በኋላ ያለው ሕይወትህ ከሐጅ በፊት እንደነበረው ላይሆን ጠንካራ ወሰኔ አብሮህ የሚጓዝ መሆኑ ነው:: ያም ተቀባይነት የማግኘቱ ምስጢር ነው:: እሱም ታላቁ አላህ ተቀባይነትን በመቸር ባከበራቸው ሰዎች መንፈስ ውስጥ ሐጅ

የሚያስከትለው ታላቅ ለውጥ ተጽእኖ ትርጉም ነው፡፡

ከሐጅ በፊት ከሶላት ወደኋላ ይል የነበረ የሐጀ ተጓዥ ከሐጅ በኋላ የጀመአ ሶላት ሊያመልጠው አይገባም፡፡ ከሐጅ በፊት የተከለከለ ነገርን እንደቀላል ነገር ይመለከት የነበረ የሐጅ ተጓዥ ከሐጅ በኋላ ፈጽሞ አይቀርበውም፡፡ ከሐጅ በፊት ዝምድናን ይቆርጥ የነበረና ለወላጆቹ የማይታዘዝ የነበረ የሐጅ ተጓዥ ከሐጅ በኋላ ከዝምድና ቀጣዮችና ለወላጆቹ እጅግ ታዛዥ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የተከለከሉ ነገሮችን ያይና ያዳምጥ የነበረ የሐጅ ተጓዥ ከሐጅ በኋላ ከነሱ በጣም የሚርቅና ከነሱም በኃይል የሚደነብር ሆኖ ይስተዋላል፡፡ ከሐጅ በፊት ይዋሽና

ያታልል የነበረ የሐጅ ተጓዥ ከሐጅ በኋላ እንደዚህ ሆኖ አናገኘውም። ወዘተረፈ... ከሐጅ በኋላ ምንም ነገር እንዳልተከሰተ ሁሉ ወደ ተከለከሉ ነገሮች እንደገና የሚመለስና አጥፊ ተላላቅ ወንጀሎች መፈጸሙን የሚቀጥል የሐጅ ተጓዥማ «ሊገለጽ የሚችለው» ይህ ነው በማይባል አስከፊ ምንድክና ውስጥ ነው። «በሚል ቃል ብቻ ነው»

አላህ ለትእዛዙ ተገዢነታችንን ይቀበለን ከኛም የሚፈጠረውን ጉድለት ይቅር ይበልልን ከሱ ዘንድ ተቀባይነት ካገኙትም ወስጥ ያደርገን።

አላህ የአክብሮት እዝነቱን፣ የማክበር ሰላምታውንና በረከቱን በነብያችን፣

**በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባለደረቦቻቸው ያውርድ፡**

**ኪንግደም ሳውድ ዐረቢያ**

**በእስልምና ጉዳዮች፣ ገንዘብ ስጦታ፣**
**ዳእዋና መምሪያ ሚንስቴር**
**የህትመትና ሳይንሳዊ ምርም**
**ድርጅት**

**መ.ሣ.ቁ**. 61843 **ኮድ** 11478
**ቴሌ**. 00966114736999
**ፋክስ** 00966114737999
**ሪያድ** info@islam.org.sa